# <u>*ሀማ ቱማን አዳምጡ*</u>
# <u>*አገርን ቶሎ አድኑ*</u>

*ከሐጎስ ቂናጢ*

*ሀማ ቱማ !*

*ሀማ ቱማ ! ወያኔ በእጅጉ የሚፈራው፣ ቀልብ አሳጥቶ የሚያባንነውና የሚያርበደብደው ያንድ አውራ ታጋይ ስም።*

*ይህ አውራ ታጋይ ባንድ ወቅት "ሀገርን እያጠፉ ላለ አረመኔ ወያኔ. . . . . . . . ቻይ መሆን ሀገርን ይጐዳል" ከሚል ግንዛቤ በመነሳት የተቃዋሚ ቡድኖችንና የወያኔን ፖለቲካ ገምግሞ ባቀረበው ጽሑፍ "ጠጣሩ እንዲላላ የላላውን ወጥረን፣ ተጠናክረን አይዞህ በርታ ተባብለን ሀገራችንን ኢትዮጵያን ከጥፋት ማዳን መቻል አለብን" በማለት መሪና ወሳኝ ሀሳብ አቅርቦ ነበር።*

*ያኔ፣ ይህን ሀሳብ እንደ አጣዳፊ ጸረ- ወያኔ ብሔራዊ አጀንዳና የትግል መስመር አድርገው የፖለቲካ ተቃዋሚዎች ሁሉ ቢቀበሉትና ተግባራዊነቱንም ሁሉን ባቀፈ ትብብር እውን አድርገው ቢያረጋግጡት ኖሮ፤ ዛሬ የላቀ፣ የደረጀና ግብ የሚያረጋግጥ ጥንካሬና የፖለቲካ ክላውት በነበራቸው ነበር።*

*ምን ይደረግ ! የፀረ- ወያኔ የፖለቲካ ተቃውሞ ችግሩ እንደ ሀማ ቱማ ዓይነቱን ጥሩ ኢትዮጵያዊና አውራ ታጋይ ምክርና ጥሪ አለመስማት ነው።*

*ይህ ሰው የልጅነት አፍላ ጊዜውን ለኢትዮጵያና ለሕዝቦቿ ጥቅሞች የሰዋ፣ በመራራና በቆራጥ ትግል ነጥሮና ጠሎ የወጣ፣ ግዙፍ የትግልና የድርጅት ተመክሮ ያካበተ፣ አስተዋይነትንና ጥበብን የተካነ ዛሬም እንደ ትናንቱ ለኢትዮጵያ የቆመ ትልቅ ሰውና አንጋፋ ፖለቲከኛ ነው።*

*የሚያቀርበው የነጠረ ሀሳብና የሚያስቀምጠው ፍቱን መፍትሔ ሁሉ በወያኔ ላይ በአስተማማኝ ድልን የሚያቀዳጅና አገርን የሚያድኑ ናቸው። በተለይ ሰሞኑን በፓልቶክ ጥያቄና መልስ የቀረበው ትንተናና አስተያየት መሬት ላይ ጠብ የማይል የትግልና የድል መመሪያ ነው።*

*ይህ አንጋፋ ታጋይና ፖለቲከኛ በዚህ ቀውጢ ሰዓት በዋነኛነት የሚጠቅም በመሆኑ እርሱንና ፖለቲካውን ማግለል ከቶ የማይቻልና የማይታሰብ ነው።*

*ኢትዮጵያን ከወያኔ እናድን ካልን የሀማ ቱማን ተመክሮና አስተያየቶች አልቀን ልናይና የግድ ልንቀበላቸው የሚገቡ ሀቆች መሆናቸውን መረዳትና ለተግባራዊነታቸውም በኅብረት መሰለፍ እንዳለብን መገንዘብ ያስፈልጋል።*

**ዝም ብሎ ማቀንቀን፣ በየፊና ለሥልጣን መቁነጥነጥና የፖለቲካ ሽውሽው የትም ስለማያደርስ አንጋፋውን ፖለቲከኛና ታጋይ ሀማ ቱማን አዳምጡ። ሀሳቡን ተከተሉ ህብረት ፍጠሩ ኢትዮጵያን አድኑ !**